ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

ፕሮግራም፡ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 25 ሜትር ባንድ

Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on 25 meter band

*የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ*
*የካቲት 18 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ*

## <u>የፓርቲው፤ ተጠያቂነትና ኃላፊነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው</u>

## <u>ለማንም ግዴታ የለበትም</u> !

ለዴሞክራሲ ሥርዓት መስፈን የሚታገል ድርጅት፤ ከማንኛው በፊት ተጠያቂነቱና ኃላፊነቱ በቀጥታ ለሕዝቡ መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው። ይህንን ካላወቀ፤ የሕዝብ አገልጋይ ሊሆን አይችልም ። ታጋይ የሚለውንም ስም ሊያገኝ አይገባውም። በሕዝብና በሀገር ስም ሲምሉ ሲገዘቱ የነበሩ ድርጅቶች፤ የሥልጣን ኮረቻ ሲቆነጥጡ፤ መሃላቸውንና ውግዘታቸውን አሽቀንጥረው በመጣል፤ ሕዝብን ሲክዱና ሀገርን ሲሸጡ እነሆ ዛሬ በገሃድ እየታየ ነው። ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን ለሕዝብ ያለማደረግ በሽታ፤ እስከ አሁን ደረስ የሀገራችንን የፖለቲካ መልከዐ-ምድር ተጠናውቶት ይኖራል ። ይህ በሽታ መወገድ አለበት፤ በውድም ይሁን በግድ !

ኢሕአፓ፤ እንደ ትግል ድርጅነቱም ይሁን እንደ ሕዝባዊ ተቋምነቱ፤ ኃላፊነቱና ተጠያቂነቱ በቀጥታ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ መሆኑን በልበ ሙሉነት ያረጋግጣል። ኢሕፓን ከኢትዮጵያ፤ ኢትዮጵያንም ከኢሕአፓ ለይቶ ለማየት የማይቻለውም በዚህ የጠነከረ ቁርኝት ነው። ይህ ኢትዮጵያዊ ልበ ሙሉነት ደግሞ የትግል አይበገሬነትን ባኅርይ እንዲጎናጸፍ አስችሎታል።

የውጭ ባዕዳንንም ይሁን የውስጥ አምባገነን ገዥዎች ሊያንበረክኩት ያልቻሉትም፤ በዚህ በኢትዮጵያዊ ባሕሪውና ይህንንም አጥብቆ በመያዙና ሕይወቱንም ጭምር ለመስዋዕት ለማቅረብ የቆረጠ በመሆኑ ነበር። አሁንም ነው። አይበገሬንትንና ቆራጥነትን ደርቦ በመያዝ የሚታገለውም፤ ለማንም ሳይንበረከክ፤ ከማንም ጥቅም ሳይፈልግ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ በመፍራትና ተጠያቂነቱንና ኃላፊነቱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ስላደረገ ነው ። በዚህ ማንነት ላይ የተመሰረተ ዕምነትን ይዞ የሚታገል ድርጅት፤ በታሪክም ሆነ በትውልድ ፊት ተወቃሽ ሊሆን አይችልም ብለው አባላቱ ያምናሉ።

በአይበገሬነትና በግትርነት መካከል ያለውን ልዩነት ካለማውቅም ይሁን፤ ወይም እያወቁ ሆን ብሎ ለማደናገር የሚሰነዘሩትን ውሽንፍሮችና ጭጋጎች መግፈፍ አስፈላጊ እንደሆኑ እንረዳለን ። በምናልባታዊ ዕሳቤ ላይ የተመረኮዙ ዝባ-ዝንኪዎችን ከመጤፍ ሳይቆጥሩ፤ በተጠያቂነትና ኃላፊነት ላይ ያተኮሩ ዕውነታዎችን ለሕዝብ መግለፅ፤ የአንድ ታጋይ ድርጅት ግዴታው መሆኑን እናምናለን ። ለኅብረተሰቡ ግልፅ ሊሆኑ የሚገባቸውን ሁሉ ይፋ ከማድረግ ፓርቲው ወደ ኋላ ብሎ አያውቅም። ወደፊትም ይህንኑ ከማድረግ አይቆጠብም ።

ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃ አውጭና ሙብትንም አስጠባቂ ድርጅት እንደመሆኑ፤ በአመለካከት፤ በራዕይና በተግባር ኢትዮጵያዊ ከመሆን በስተቀር ሌላ መለያ ሊኖረው አይችልም። በመሆኑም፤ ጠላትን

በመለየትና በመቋቋም፤ በመከታተልና በማጥቃት ከሚያደርገው ውጭ፤ ከኅብረተሰቡ ጋር የሚያደርጋቸው ግንኙነትና ተግባራት፤ የሚያወጣቸው ጽሁፎችና መግለጫዎች ሁሉ ግልፅነትንና ቀጥተኛነትን የተላበሱ ሆነው ቆይተዋል ። ወደፊትም፤ ይህንኑ ባኅርይ ይዘው ይቀጥላሉ ።

የፓርቲው ታዋቂ ( ኦፊሴላዊ ) ልሳኑ ዴሞክራሲያና ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ የድርጅቱን መግለጫዎች፤ ፖሊሲዎች፤ መመሪያዎች፣ ማስታወቂያዎች፤ ሰነዶች፤ አዋጆች፤ ወዘተ… ለሚታገልለት ሕዝብ የሚያሳውቅበት ልሳኖቹና መድረኮቹ ናቸው። በመሆኑም፤ በእነርሱ ላይ የሚወጡት ማነኛቸውም ጽሁፎችና የሚተላለፉት መልዕክቶች ላይ ፓርቲው ኃላፊነትና ተጠያቂነት ይኖረዋል። በሌሎች መሸረፊቶችና ሰፌዶች ላይ የሚራገቡትና የሚናፈሱት ሁሉ ፓርቲውን አይመለከተውም ።

ሹሮው ያረረበት ሁሉ፤ ያሰረረብኝ ኢሕአፓ ሳይሆን አይቀርም ብሎ ከሚጨነቅ ይልቅ፤ የማዕድ ቤቱን ይዞታና የመገልገያ ቆሳቁሱን ዓይነት ሊፈትሽ ይገባዋል ።

ዛሬ፤ በቴክኒዮሎጅ ዕድገት፤ ምጥቀትና ስፋት ምክንያት፤ የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎትና ስርጭት ከአድማስ እስከ አድማስ ኅብረተሰቡ ይጠቀምበታል፡፡ የዓለምን ሕዝብ አቀራርቦታል። ዕውቀት፤ ትምህርት፤ ቆሳቆስ፤ ሳይንስና መርጃዎች ይዘዋወርበታል ። ይሰራጩበታልም ። ይህ ከስተት የሚጠቅምና የሚወደድም ነው ፡፡ ሊበረታታና ለደገፍም ይገባል ። ማኅበራዊ መገናኛ ( ሶሻል ሚዲያ) የሚያበረክቱት አግልግሎት በቀላሉ አይገመትም ። ይህንን የሥልጣኔ ርምጃ ማንም በባለቤትነት በግል ይዞታ ሊቆጣጠረው አልተቻለውም ። ቢሞክርም አይሳካለትም ።

" ዕውቀት የሁሉም ነች ባለቤት የላትም ፤

ተጠቃሚው ሁሉ ይጠቅማል የትም ! "

መባሉ፤ ዕውቀትን ለሚፈልጋት፤ ሁሉንም ያለአድሎ ትጠቅማለች እንጅ፤ ማንም የግል ሀብቱ ንብረቱ አድርጎ በብቸኝነት ለራሱ ብቻ ሊያደርጋት አለመቻሉን ያረጋግጣል ። ጥበብን፤ ሳይታክት የሚፈልጋት ሁሉ ያገኛታል ። ይጠቀምባታልም !

በአሁኑ ወቅት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመጠኑም ቢሆን፤ በሀገር ቤት ደረጃ፤ ይህንን የቴክኒዮሎጅ ዕውቀትና አገልግሎት፤ ከሞላ-ጎደል እንደሚጠቀምበት ተስፋ ይደረጋል። ኅብረተሰብ፤ እርስ በእርስ በሚያደርገው ግንኙነት ብዙ የኃሳብ ልውውጥ በማደረግ በኩል ተጠቃሚ ይሆናል ተብሎ ይገመታል፡ የዚህ አስተጋብኦ፤ ስፋት ያለው እንቅስቃሴ ለማድረግ ሚና ይኖረዋል። የሶሻል ሚዲያ እንቅስቃሴ፤ ዐረቦቹ፤ አምባገነኖችን ለማወረድ አስችሏቸዋል። በእኛ ሀገር፤ ተመሳሳይ ውጤት ሊያስመዘግብ የማይችልበት ምክንያት አይኖርም። በተቀነባበረ መልኩ ከተሰራበት ! በቀጣይነት ሳይታክቱ ከተጠቀሙበት !

የግል ባለቤት ሳይኖረው ሁሉም በየፈናው በሚፏልልበት መድረክ ሁሉ፤ አንድን ድርጅት ለይቶ በመጥቀስ፤ በኃላፊነት ለመፈረጅ መሞከር ምክንያታዊ አልባ ከመሆን አይዘለም። ድረ-ገፆች፤ የመድረክ ውይይቶች፤ የሃሳብ መለዋወጫዎች፤ ፌስ ቡኮችና፤ ሌሎች መድረኮች ሁሉ አገልግሎታቸው የሚደገፍ ቢሆንም፤ በሁሉም

መድረኮች፤ የአንድ ድርጅት እጅ ሳይኖርበት አይቀርም ብሎ መብሰልሰል፤ ከንቱ ድካም ይሆናል። ሁሉም በየፊናው፤ በተለያዩ መድረኮች፤ የሃያ አራት ሰዓት አገልግሎት በመስጠት ሕዝቡን ማወያየት የሚደገፍ ቢሆንም፤ ለሁኔታው ተጠያቂና ኃላፊነት የሚውስደው፤ መድረኩን የሚቆጣጠረው ቡድን ብቻ ነው የሚሆነው። ሌላው ክፍል ፤ ባልገባበት፤ ባልተቆጣጠረውና ባልተመለከተው ጉዳይ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም ። ይህ ደግሞ፡ የመብታና ግዴታ፤ የተጠያቂነትና ሃላፊነት ግንዛቤና ትምህርት ሀሁ ነው። የአንዱን ባለቤትነትና ኃላፊነት በቀጥታም ይሁን በአንደምታ፤ ወደ ሌላ መላከክ፤ " ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ " ነው ። ቢንከራተቱ አያገኙትም ። ቢወረውሩበትም አይመቱትም ። አያጠቁትም !

ድርጅቱን የሚጠሉትና የሚፈሩት ሁሉ፤ ፓርቲውን ያጥላሉት እየመሰላቸው፤ ብሎም፤ ትግሉም ይሰናከላል ብለው ስለሚያስቡ፤ ብዙ ይደከማሉ። በድረ ገፆችና የውይይት መድረኮች ፤ የሚፃፉትንና የሚነገሩትን ሁሉ የፓርቲው ሳይሆኑ አይቀሩም ብሎ መገመት ከጤነንነት የሚመነጭ ሀሳብ አይሆንም። ፓርቲውን፤ የሁሉም አቅጣጫ ሰጭ፤ ተቆጣጣሪና አራጊ- ፈጣሪ አድርጎ መገመት፤ ከፍርሃትና ከጥላቻ የሚመነጭ ዕኩይ ባኅርይና አደገኛ ጠባይ ከመሆን አይዘልም ። ሁል ጊዜ፤ ፍርሃትና ጥላቻን አንግቦ የሚኖር፤ በመጨረሻ የራሱ አጥፊው ራሱ ነው። ሁሉንም ነገር ኢሕአፓ ይሰራዋል፤ ያደርገዋል፤ ይቆጣጠረዋል፤ ያጠፋዋል፤ ያበላሸዋል ወዘተ ብሎ ማሰብ፤ በመሠረቱ ሦስት ችግሮች አሉት ።

አንደኛው፡- ፓርቲው፤ የሌለውን ችሎታና ኃይል እንደመስጠት ነው። ይህ ደግሞ፤ እንደ ሃይማኖት መሪዎች አስተምህሮ ፤ መለኮታዊ ባኅርይና ክኅሎት እንዳለው አድርጎ መቆጠር ይሆናል። " አምላክ በጊዜና በቦታ አይወሰንም " ብለው የሃይማኖት አባቶች ያስተምራሉ። በዚህ ዕምነት መሠረት፤ በሁሉም ቦታ፤ በአንድ ጊዜ፤ ሊገኝ የሚችለው ፈጣሪ እንጅ ሰዎች የፈጠሩት ኢሕአፓ ሊሆን አይችልም ። ፓርቲው፤ ለሁሉምና ለማነኛው ጉዳይ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም። አይገባውምም !

ሁለተኛው፡- ሁሉንም፤ ኢሕአፓ ይቆጠጠረዋል፤ ያዝዘዋል፤ ይነደዋል፤ ይጎተተዋል፤ ብሎም፤ በየመድረኮቹ የሚወጡትና በሁሉም ቦታዎች የሚጽፉት ሁሉ የኢሕአፓ እጅ አለበት ወዘተ ብሎ ማሰብ፤ የሌላውን ሰው የማሰብ ችሎታ መናቅና ሰብዕናውንም መዳፈር ይሆናል። የሁሉንም ሰው አዕምሮ ብቃትና ብስለትን መናቅም ነው። ይህ አመለካከት ደግሞ፤ በሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን እኖራለሁ በሚል ግለሰብም ይሁን ማኅበረሰብ ተቀባይነት አይኖረውም። በዕርግጥ በድንጋይ ዘመን መኖርን እንፈልጋለን ካልተባለ በስተቀር!

ሦስተኛ፡- አጠቃላይ የሀገሪቱን ችግሮች ሁሉ ያመጣው እርሱ ነው በማለት፤ ፓርቲውን ለመሥዋዕት ጠቦት ለማቅረብ ሲምከር የነበረው ከንቱ ጥረት ሁሉ ዉሃ ያልቋጠረ ስለነበር ፤ የዉሃ ሽታ ሆኖ መቅረቱን ይኸው ታሪክ እየመሰከረ ነው ። ወትሮውም ቢሆን ሙከራዎቹ ሁሉ፤ በስሜ-በለውና በአሉ-ባልታ ሽኩሹክታ የተሰራጩ ስለነበሩ፤ እነሆ ዛሬ ዕውነቱ እየተከሰተ፤ ታሪክም የሃቅን አድማስ እያፈጋው ይገኛል። " የወሬ የለው ፍሬ ፤ የአበባ የለው ገልባ " እንደተባለው፤ በዚህ ሥነ- ልቦና የተበከለ ሁሉ መጥኔ የሌለው ፍሩሽካ ሆኖ ይቀራል።

ሀገሪቱ፤ በጠላቶቿ ስትጠቃ አጋፍጠዋት የሄዱትንና በመከራዋ ጊዜ ከጉኗ ቆሞ አጥፊዎቿን የሚታገለው ማን እንደሆነ ዛሬ ተለይቶ ታውቋል። ለዚህ ሃቅ ደግሞ ማስረጃ ልናቀርብ አንገደድም ። ኢትዮጵያን ለማዳን በሚደረገው ትግል፤ ግንባር-ቀደም ሆኖ ከመዋደቅ በስተቀር፤ ተንኮለኞች በሚያደርጉት የመሥዋዕት ጠቦት ፍለጋ ሰለባ ሊያደርጉን አይችሉም ። ኢትዮጵያን ለማዳን በግድ የመሥዋዕት ጠቦት ማቅረብ አስፈላጊ ከሆነ ግን ኢሕአፓ የመጀመሪያው ይሆናል ።

ግራም ነፈሰ ቀኝ፤ ፓርቲው በዕርግጠኝነት አምኖና ተቀብሎ፤ በመርኀ ደረጃ አንግቦ የያዛቸውን መተከላዊ አቋሞችና የትግል መርኀዎች፤ እንዲሁም ለሕዝብ የገባቸውን ቃል-ኪዳኖችና ሀገራዊ ራዕይ፤ ዕውን እንዲሆኑ፤ በፅናት ከመታገል ወደ ኋላ አይልም። በሚያገኘው መድረክም ይሁን በትግል ሜዳ፤ የመጀመሪያ ዒላማው፤ ዘረኛው ሥርዓትና የሥርዓቱ አራማጆች ናቸው። ይህንን ከማድረግ ደግሞ፤ የማንም ጥላቻና ፍራቻ አያግደውም። የማንንም ፈቃድ አይጠይቅም። ወያኔ በሚወገዘበትና በሚጠቃበት መድረክ ሁሉ ፓርቲው በአካልም በመንፈስም አለ። ይኖራልም። በአሉባልታና በአስመሳዮች ጨረባ ተስካር ከመገረም በስተቀር፤ ስለ እነርሱ ማንነት አይጨነቅም። ትግላችን ፀረ ወያኔ ነው። ትኩረታችን በዚህ የሕዝብ ጠላት ላይ ነው ። በጎን ርዕሶች፤ በግርጌ ማስታዎሻዎችና አሳሳች ተልዕኮ አራማጆች ላይ የምናጠፋው ጊዜ አይኖረንም ።

የሚከተሉትን ዕውነታዎች ለግንዛቤ እናሰፍራለን፡------

ሀ/ ፓርቲው፤ ተጠያቂነቱ፤ ኃላፊነቱና ግዴታው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው ።

ለ/ ድርጅቱን እንደ መሥዋዕት ጠቦት ለመጠቀም የሚሹትን ሁሉ አምርሮ የይቋቋማቸዋል። ይታገላቸዋልም !

ሐ/ ኢትዮጵያን ለማዳን የመሥዋዕት ጠቦት ያስፈልጋል ከተባለ ግን ኢሕአፓ፤ ለመሥዋዕትነት የመጀመሪያው ይሆናል ።

መ/ በሀገሪቱ ውስጥ ለቆየውም ሆነ አሁን ላለው ችግር ፓርቲው ተጠያቂ ሊሆን አይችልም ። ተጠያቂነቱ ግን ፤ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት/ አስተዳደር ለሚደነገግ ሕግ ፤ ለሕዝብ፤ ለትውልድና ለታሪክ እንደሆነ ያምናል። ይቀበላል ።

ሠ/ የሀገራችንን ስትራተጂያዊ ጥቅምና ሀገራዊ ደህንነት የሚጎዱትን ሁሉ፤ እየተከታተለ ይዋጋቸዋል። ለዚህም መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጎኑ እንዳለ ያምናል ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !